Amharisch




## በራሪ ወረቀት

# የቋንቋ ብዝሐነት በቤተሰብ ውስጥ

*ልጅዎት ከአንድ በላይ ቋንቋ በሚነገርበት ሁኔታ ውስጥ ነው የሚያድገው? እንኳን ደስ አለዎት፡- በዚህ ሁኔታ የተለየ ዕድል ሊፈጥሩለት ይቻልዎታል! ከአንድ በላይ ቋንቋ በሚነገርበት ሁኔታ የሚያድጉ ልጆች ተጨማሪ ቋንቋ በቀላሉ ለመማር ይችላሉ በዚህ ላይ እርስዎም ልጅዎን ሊያግዙ ይችላሉ።*

# የቋንቋ ብዝሐነት በቤተሰብ ውስጥ

Amharisch

## በቤተሰብ ውስጥ የትኛውን ቋንቋ ነው መናገር የሚገባው? - የወላጆችን የአፍ መፍቻ ቋንቋ።

እናቶች፣ አባቶች ወይም ደሞ ሌላ የቤተሰብ አባል በደንብ በሚችሉትና በሚግባቡበት ቋንቋ ልጆቻቸውን ቢያነጋግሯቸው ይመረጣል፡ ፡ ይህም ማለት ልጆቻቸውን በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ቢያናግሯቸው የተሻለ ነው። ልጆችዎ የእርስዎን የአፍ መፍቻ ቋንቋ በደንብ እንዲማሩ እርስዎን በምሳሌነት ሊያዩ ያስፈልጋቸዋል። ይህን በማድረግም ሌላ አዲስ ተጨማሪ ቋንቋ መማር እንዲችሉ መደላድል ይፈጠርላቸዋል።

## ልጆች በቋሚነት መዋለ ህጻናት መሄዳቸው ጀርመንኛ ቋንቋ በቀላሉ እንዲማሩ ይረዳቸዋል!

ልጅዎት መዋዕለ ሕጻናት በሚገባበት እድሜው ላይ ጀርመንኛ ቋንቋ በብቃት አለመናገሩ ሊያሳስብዎት አይገባም። በዚህ ሁኔታ ላይም እርስዎ አሁንም ከልጆችዎ ጋር ቤት ውስጥ በአፍ መፍቻ ቋንቋ መነጋገሩን ይቀጥሉ፡
፡ ልጅዎት ከአስተማሪዎቹና  ከሌሎች ልጆች ጋር በሚኖረው ግንኙነት የጀርመን ቋንቋ ይማራል። ይህም እንዲሳካ ልጅዎት በቋሚነት መዋዕለ ሕጻናት መሄድ ይገባዋል። ልጅዎት ጀርመንኛ ቋንቋ ከሚናገሩ ልጆች ጋር:- እንደ መዋዕለ ሕጻናት፣ የልጆች መጫወቻ ቦታ፣ የስፖርት ክለቦች ውስጥ እየተጫወተ በሄደ ቁጥር ሳይታወቀው ጀርመንኛ ይማራል።

## ልጆች ቋንቋ ያደባልቃሉ ወይም ደሞ ያቀያይራሉ!

ልጆች አንድ አዲስ ቋንቋ በሚማሩበት ጊዜ መጀመሪያ  አካባቢ የተለመደ ስሕተት ይሰራሉ። ይህ የሚሰሩት  ስህተትም ጀርመንኛ ቋንቋን በትክክል እየተማሩ እንደሆነ ማሳያ ነው። ለምሳሌ በጀርመንኛ ሲናገሩ አርቲክሎችን አይጠቀሙም („gib mir das Blatt“ ከማለት ይልቅ “gib mir Blatt“ ይላሉ) ወይም ደሞ ፕሪፖዚሽን ላይ ስህተት ይሰራሉ („auf dem Baum“ ከማለት ይልቅ„beim Baum“ ይላሉ)። ብዙ ጊዜ ከአንድ በላይ ቋንቋ እየተናገሩ የሚያድጉ ልጆች ለረጅም ጊዜ ሁለት ቋንቋዎች ይደባልቃሉ። ለምሳሌ ያህል:- „እኔ Ball አለኝ“ ሊሉ ይችላል። ይህም ቋንቋ የመማር ችሎታቸው የዳበረ እንደሆነ ያሳያል። በጉዳዩ ላይ እርገጠኛ ካልሆኑ ወይም ደሞ የምክር አገልግሎት የሚያስፈልግዎት ከሆነ የመዋዕለ ሕጻናት አሳዳጊዎችን ወይም ደሞ የልጆች ሐኪም ያማክሩ።



## ልጄ በድንገት ከጀርመንኛ ውጪ ሌላ ቋንቋ መናገር አቆመ!

አንዳንድ ወላጆች ልጆቻቸው በሆነ ወቅት የቤተሰቦቻቸውን ቋንቋ ለመናገር እንደማይፈልጉና በጀርመንኛ ብቻ እንደሚያወሩ ሲናገሩ ይደመጣሉ። ይህ ምንም ሊያሳስብ የሚገባ ጉዳይ አይደለም።ይህ ቢያጋጥምም እናንተ ልጃችሁን አሁንም በራሳችሁ አፍ መፍቻ ቋንቋ ማዋራታችሁን ቀጥሉበት። ልጃችሁ የቋንቋው ችሎታውን በመስማትም ብቻ ቢሆን ሊያዳብር ይችላል፤ ከዛም በርግጠኝነት አንድ ቀን እንደገና መናገር መጀመሩ አይቀርም።

## ማውራት ያስደስታል!

ከልጅዎት ጋር ብዙ ጊዜ እንዲሁም በተደጋጋሚ ስላጋጠመው ነገር ያውሩት። ታሪክ ይንገሩት፣ መጽሐፍ ያንብቡለት ወይም ደሞ አብራችሁ ተጫወቱ። ከልጅዎ ጋር የሚያደርጉት ማንኛውም አይነት ግንኙነት በቋንቋ ችሎታው ላይ አዎንታዊ ተጸዕኖ ይፈጥርለታል። ያጋጠሙ ነገሮችንና ተሞክሮዎችዎን በማቀናጀት በአፍ መፍቻ ቋንቋው እያገናኘ እንዲናገር ማድረጉ የቋንቋ ክህሎቱን ለማዳበር ይረዳዋል።

## ብዙ ቋንቋ እየተናገሩ ማደግ ጥሩ አጋጣሚ ነው!

ልጅዎ በተገኙት አጋጣሚዎች ሁሉና በተደጋጋሚ የቋንቋ ክህሎቱን መጠቀም የሚችልበትን ሁኔታ ቢፈጥሩለት የቋንቋ ክህሎቱን በቀላሉ ማዳበር እንዲችል ያሥችሉታል። የዕርስዎ የአፍ መፍቻ ቋንቋና ባሕል እንዲሁም የዚህ አካባቢ ቋንቋ የሆነው ጀርመንኛ ቋንቋ ለልጅዎት ትርጉም ያለው ጉዳይ ሊሆኑለት ይገባል። ልጅዎት ማንኛውም ቋንቋ ሊሰጠው የሚችለውን ጥቅም የሚገነዘብበት ደረጃ የወላጆቹንም አፍ መፍቻ ቋንቋ ሆነ የጀርመንኛ ቋንቋን ለመጠቀምና በቀላሉ ለመማር በጣም ጠቃሚ ነው። በዚህም ልጅዎትን ለመዋዕለ ሕጻናትም ሆነ ትምሕርት ቤት ዝግጁ ያደርጉታል።

LakoS
Landeskompetenzzentrum zur sprachlichen Bildung und Förderung an Kindertageseinrichtungen in Sachsen

Weitere Informationen finden Sie unter:
www.lakos-sachsen.de

Diese Maßnahme wird mitfinanziert durch Steuermittel auf der Grundlage des vom Sächsischen Landtag beschlossenen Haushaltes.

SACHSEN